የኢትዮጵያ ዘውድ ምክር ቤት
THE CROWN COUNCIL OF ETHIOPIA

# የኢትዮጵያ ዙፋን የኢትዮጵያን አንድነትና የህዝቦቿን ሕብረት ጉዳይ ረስቶ አያውቅም

ከክቡር ልዑል ኤርሚያስ ሳህለ ሥላሴ ኃይለ ሥላሴ፤ የኢትዮጵያ ዘውድ ምክርቤት ፕሬዘዳንት

ዋሺንግተን ዲሲ፤ የካቲት 28 ቀን 2010 ዓ.ም

የኢትዮጵያ ዘውድ ምክርቤት፤ በኢትዮጵያ ወስጥ የሚታየውን የመከፋፈልና የማለያየት ጥረት፤ በጥልቅ ሐዘን እየተከታተለው ነው። የሚገርመው፤ ይህ ድርጊት በመካሄድ ላይ ያለው፤ የታላቁን የአድዋ በዓል 122ተኛ ዓመት እያከበርን ባለንበት ወቅት ነው።

የኢትዮጵያ ዙፋን፤ በኢትዮጵያ ወስጥም ሆነ ወጪ በመካሄድ ላይ ባለው ፖለቲካ ወስጥ ጣልቃ የመግባትም ሆነ ፍርድ የማስጠት ፍላጎት የለወም። እንዲያውም፤ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፤ የዙፋኑን ስልጣን ህገ-መንግሥታዊ ለማድረግና የፖለቲካ አስተዳደሩን በህዝብ ለተመረጡ ኢትዮጵያወያን ለማስረከብ ዕቅድ እንደነበራቸውልናስገነዝብ እንወዳለን። እኛምልጆቻቸው፤ የአባባ ጃንሆይን ቃል ለማጠበቅ ዝግጁነን።

በድጋሜ ማረጋገጥ የምንፈልገው፤ የኢትዮጵያ ዘወድ ምክርቤት፤ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ህዝብ ያለውን ሀላፊነትና ቃል-ኪዳን፤ ምን ጊዜም ቢሆን ረስቶ አለማወቁን ነው። ምንምእንኳን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፤ ህጋዊ ባልሆነ የወታደራዊ ሜንቅለ-መንግስት ከሥልጣን ቢነሱምና በኋላም ቢገደሉም፤ እኛም ሆንን የኢትዮጵያ ህዝብ፤ ለሀገራችን ያለንን ታሪካዊ ሀላፊነት ምንጊዜም መተውና መርሳት አይገባንም።

የኢትዮጵያ ዙፋን፤ በኢትዮጵያ ዘወድ ምክርቤት በኩል፤ በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል የተፈጠረውን የመከፋፈልና የአለመግባባት ችግር እንዲወገድ ለማድረግና አስማሚ ሀይል ሆኖ ለማገልገል ዝግጁ ነው። የእኛ አቋም፤ በዘር፤ በሃይማኖትና በክልል ላይ ያልተመረኮዘ በመሆኑ፤ የሁሉንም ኢትዮጵያዊ መብት ጠባቂና የኢትዮጵያን ታሪካዊ ድንበር አስከባሪ የመሆን አመቺ ሁኔታ ይፈጥርልናል።

የኢትዮጵያ ዙፋን፤ የሀገራችንን አንድነትና ክብር ለማስጠበቅና ሸብራቃ ባህሎቻችንም የሚኮሩን እንጂ የሚለያዩን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ ወደ ኋላ አይልም። ከ3ሺ ዓመታት በላይ ዕድሜ ያለው የሰለሞናዊው ዙፋን፤ ወደፊትም የኢትዮጵያ ክብርና መመኪያ መሆኑን ይቀጥላል። የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ፤ ዙፋኑ አልረሳችሁም። እናንተን ለማገልገል አሁንም ዝግጁ ነው። በኢትዮጵያ ወስጥ፤ ዲሞክራሲና ፍትህ እንዲሰፍንና ኢትዮጵያወያን የመረጡትን የፖለቲካ ሂደት እንዲከተሉ የዙፋኑ ምኞትና አቋም ነው። የመንግሥት ሀላፊነት የህዝብን ፍላጎት ማጠበቅ ሲሆን፤ የዙፋኑ ተልዕኮ ደግሞ መንግሥት ለህዝብ የገባውን ቃል እንዳይረሳ ማድረግ ይሆናል።

ቸሩ እግዚአብሐር ኢትዮጵያን ለዘላለም በሰላም ይጠብቃት።